ዴሞክራሲያ ቅፅ 33 ቁ. 5 የካቲት 2000 ዓ.ም.

## መልዕክተ የካቲት

በሀገራች የአያሌ ዘመን ታሪክ ሂደት ውስጥ፣ ዐቢይ የታሪክ ምዕራፍ ከያዙት ክስተቶች አንዱ የየካቲት ስድሳ ስድስቱ አብዮት ለመሆኑ፣ ማነኛውም ዜጋ በኩራት የሚያስታውሰው ነው:: ይህ ታሪካዊ አብዮት፣ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የመራራ ትግል ማህፀን ተፀንሶ ከረዥም ዘመን የብዝበዛና የጭቆና ሥርዓት ተረግዞ፣ በአንድ ትውልድ የአመፅ እንቅስቃሴ የተወለደ ኢትዮጵያዊ አብዮት ነበር:: መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ እንደ ጥንት እንደ ጧቱ ሁሉ፣ በብሔር፤ በሃይማኖት፣ በቋንቋ፤ በክፍለ ሀገር፣ ሳይከፋፈል፣ ዕምነቱን አጠንክሮ፣ አንድነቱን አስከብሮ፣ ኢትዮጵያዊነቱን አስረግጦ፣ እንደ አንድ አካል- አንድ አምሳል ቆሞ፣ በአንድ መንፈስ በአንድ ልሳን ተናግሮ፣ የነበረውን የፈላጭ ቆራጭ ሥርዓት ተቃውሞ፣ ለአዲስ ሥርዓት ለአዲስ ህይወት በኅብረት የቆመበት፣ ብሔራዊ ራዕዩን ያሳየበት ታሪካዊ ወቅት ነበር:: እውነትም አብዮት!

በዛሬው የካቲት 2000 ዓም የምናስታውሰው የስድሳ ስድስቱ የካቲት የኢትዮጵያ ሕዝብ አንጡራ ብሔራዊ አብዮታችን ፣ኢትዮጵያዊነታችንን በማያሻማ መልኩ እንደገና ለዓለም ያስመሰከርንበት በመሆኑ፣ ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን ልዩ ትርጉም ይሰጠናል:: ይህንንም ለማለት የምንችለው፣ የየካቲት 66 አብዮት እንደ ሸቀጥ ዕቃ ከውጭ ተገዝቶ፣ ወይም ደግሞ፣ በብድር - በትውስት ያልመጣ፣ ነገር ግን ፣ከኢትዮጵያ የግፍ አገዛዝ ማኅፀን የተወለደ በመሆኑ ነው:: ይህ የየካቲት አብዮት ከፈነዳ፣ ይኸው ዛሬ ሠላሳ አራት ዓመት ዕድሜ ያስቆጠረ ቢሆንም፣ የተነሳበትን ዓላማ ግን እስካሁን ሙሉ በሙሉ አልመታም:: አብዮቱ ይዟቸው ከተነሳቸው ዋና ዋና ጥያቂዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ አልተመለሱም:: ባለመመለሳቸውም፣ ዳግማዊ የካቲትን የሚጠይቅ አርዕድ-አንቀጥቅጥ ሕዝባዊ አመፅ ትግል እንደሚያስፈልግ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ይረዳዋል:: ጊዜ ቢፈጅም ደግሞ ይህ የሕዝብ ቁርጠኛ አመፅ መፈንዳቱ እንደማይቀር የታሪክን ሂደት የተረዳው ማነኛውም ዜጋ አይጠራጠርም:: ዳግማዊው የካቲት በኢትዮጵያ ሕዝብ በራሱ ቁጥጥርና አመራር ከዋለ ደግሞ፣ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንደሚመሠረት ዜጎች በዕርግጠኝነት ይተማመናሉ::

የየካቲት አብዮት፣ በበርካታ የዓለም ሀገር ሕዝቦች እንደተከናወኑት ልዩ ልዩ አብዮቶች ግቡን ሊመታ ያልቻለበት ዋናው ምክንያት፣ የነቃ የበቃ፣ የተደራጀ ፣ የተዘጋጀ፣ ኢትዮጵያዊ መሪ ድርጅት በማጣቱ ነበር ቢባል፣ ስህተት ነው ብሎ የሚከራከር ማንም የለም:: የነቃ የበቃ፣ የተደራጀ የተዘጋጀ፣ ኃይል ባለመኖሩ ምክንያት፣ ጥቂት የፊውዳሉ መኮንንችና ንዑሳን ተባባሪዎቻቸው ተመሳጥረው፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ አብዮት ጠለፉት:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓይኑ እያየ፣ ጆሮው እየሰማ በገዛ አብዮቱ ተጠቃ፣ ተጎዳ፣ ተጨፈጨፈ፣ እንደ ጭዳ ታረደ:: በስንት መሥዋዕትና ትግል ያመጣውን አብዮት ተነጠቀ:: ያን ሁሉ መሥዋዕትም ተከፍሎ አብዮቱ ግቡን ሳይመታ ቀረ:: አብዮቱን ጠልፈው ለግል መጠቀሚያ ያደረጉት ክፍሎችም የሠሩትን ሠርተው ሀገሪቱን ለበላዒ ሰብ በማስረከብ ሕዝቡን አጋልጠው በየፊናቸው ተበታትነው ከሰሙ::

በመጨረሻም ወንጀለኞቹ ፈርጥጠው ቢሄዱም፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን እስከ አሁን ከዕምነቱ፣ ከአኩሪ ታሪኩ፣ ባህሉ፣ ከሰብዕናው ከወደፊት ተስፋው ጋር ቆይቷል። ወደፊትም ይኖራል።

በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች በየትኛውም ሀገር የሚኖሩ ሕዝቦች፣ ከቅኝ ግዛት ቀንበር ነፃ ለመውጣትም ይሁን ፣ ከውስጥ ከተነሱ የአምባገነኖች ጭቆና አገዛዝ ለመላቀቅ፣ ሕዝባዊ አብዮት እያካሄዱ ዓላማዎቻቸው ግብ እንዲመቱ አድርገዋል። ዓላማዎቻቸው ግብ እንዲመቱ ካስቻሏቸው ዓይነተኛ አብነቶች መካከል፣ የአብዮቱ መሪ ድርጅቶች፣ ከሁሉ በፊት፣ የሕዝባቸውን የልብ ትርታ በሚገባ ያዳመጡ፣ ባህሉንና መስተጋብሩን ከልብ የተረዱ፣ የሀገራቸውን ታሪክ ያጠኑ፣ ክብርን ነፃነቱን ያከበሩ ያስከበሩ፣ እንዲሁም አምጡ ድገሙ የማይባልላቸው ቀናዒ ሀገር ወዳዶች ስለነበሩ ነው። በአንድ ሀገር ታሪክ፣ ባኅልና ዕምነት ላይ የተመሠረተ አብዮት የፀና እንደሚሆን ምንም ጥርጥር አይኖርም። ምንም እንኳ በተለያየ መልካቸው የራሳቸው በኅርይና የጀርባ ታሪክ ቢኖራቸውም፣ ብሎም፣ ከሀገራችን ከየካቲቱ አብዮት ጋር የንፅፅር ውስንነት ሊኖረው መቻሉን ብንረዳም፣ ከጠቅላላ የአብዮት ባኅርይ ሂደት አንፃር ሲገመገም፣ የእኛውም የየካቲቱ አብዮት፣ በሌሎች ሀገሮች ከተካሄዱት አብዮቶች ጋር ተመሳሳይነት አለው ለማለት ይቻላል። በዚህ ተመሳሳይ ነባራዊ ሁኔታ ማመን ካለብን ፣ እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር በ1789 የተካሄደው የፈረንሳይ አብዮት፣ በ1917 የተካሄደው የሩሲያ የጥቅምት አብዮት፣ ከዚያም በፊት በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ አሜሪካኖች ከእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ነፃ ለመውጣት ያካሄዱት የአሜሪካ አብዮት፣ ሁሉ ሲገመገሙ፣ ከሀገራችን የየካቲቱ አብዮት ጋር በባኅርይ ተመሳሳይ ናቸው። ልዩነቱ፣ የሀገራች አብዮት፣ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ባለቤትነት ተነጥቆ በባዕዳን እጅ መውደቁ ብቻ ነው። በዚህ መሠረታዊ ልዩነት ሳቢያ፣ የካቲት አብዮት የታለመለትን ብሔራዊ ግብ ከመምታት ተደይኖ ቀረ። ምናልባት ከዚህ ጋር ተያይዞ መገምገም ያለበት ሐቅ ቢኖር፣ የኢትዮጵያ አብዮት፣ በሰው ሕይወት መጥፋት ሲመዘን ፣ ከፍተኛ የሆነ እልቂት ያስመዘገበ መሆኑ ነው። የፈረንሳዩ አብዮት በበኩሉ የበርካታ ዜጎች ሕይወት ቢጠይቅም፣ ፈረንሳዮች ቢያንስ፣ አብዮታቸው አንኅቦ የተነሳውን የፍልስፍና መርህ፣ ማለት ነፃነት፣ እኩልነትና ወንድማማችነት በታሪክ አሻራ አስመዝግበው አለፈዋል። አለመታደል ሆኖ ግን የእኛው የየካቲት አብዮትም በበኩሉ፣ ዓላማ አድርጎ የተነሳው ማለትም ነፃነት፣ የዜጎች እኩልነትና የዴሞክራሲ ሥርዓት፣ የአብዮታችን ራዕይ ፍልስፍ የነበረ ቢሆንም፣ ሁሉም በአገር በቀል ፋሽስቶች ተረግጠ ቀረ። በዛሬይቱ ኢትዮጵያ፣ ነፃነት ወደባርነት፣ ዕኩልነት ወደ ጎሳ አድላዊነት፣ ወንድማማችነት ደግሞ ወደዘር ጥላቻነት ተለዋውጧል። የዲሞክራሲ፣ ሥርዓትም የማይዳሰስ የማይጨበጥ ህልም ሆኖ ቀርቷል። ይህ ክስተት የየካቲቱ አብዮት ዓላማና ግብ ፈጽሞ አልነበረም። እልፍ አዕላፍ የሀገሪቱ ዜጎች ሕይወት የተገበረበት የየካቲት 66 ዓም አብዮት፣ ከሠላሳ አራት ዓመት በኋላ ኢትዮጵያ ያለችበትን የአሁኑ ሁኔታ በደንብ ላጤነ አስተዋይ ዜጋ፣ የቱን ያህል የኅሊና ሰቆቃ እንደሚያጠቃው መካድ አይችልም።

የየካቲት አብዮት፣ ካነሳቸው ዋና ዋና ጥያቄዎች መካከል፣ መሬት ለአራሹ፣ የሰብዓዊ መብቶች ይከበሩ፣ የሃይማኖት እኩልነት ይከበር፣ የዜጎች ዕኩልነት ይረጋገጥ፣ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መስፈን ለኢትዮጵያ ሕዝብ መሠረታዊና አንገብጋቢ ነው የሚሉትና የመሳሰሉት ነበሩ። ለእነዚህም የሰው ልጅ መሠረታዊ መብቶች መከበር ከፍተኛ መሥዋዕት እንደከፈለ፣ ከእርሱ ከእራሱ ከባድ የሕይወት ዋጋ ከከፈለው ከኢትዮጵያ ሕዝብ የበለጠ ማንም የሚያውቅለት የለም። የወያኔ መሪዎች በወቅቱ በሕዝቡ ትግል ኅራ ስላልነበሩ፣ ይህንን ታሪካዊ ሐቅ ይገነዘቡታል ተብለው አይጠበቁም። ይልቁንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመሠረታዊ ነፃነቱ፣ ለሰብዓዊ መብቱ፣ለኢኮኖሚ ዕድገቱና ብልጽግናው፣ ለሉዓላዊነቱ፣ ለአንድነቱ ለብሔራዊ የግዛት መከበር፣ ከባድ መሥዋዕት እየከፈለ በሚታገልበት ወቅት፣ የወያኔ መሪዎች የጠባብ ብሔረተኛ ሴራቸውን እየጎነጎኑ፣ ሀገራችን እንድትጠፋ ግንባር ቀደም ሚና ይጫወቱ ነበር። በመሆኑም፣ እነ መለስ ዜናዊ፣ የየካቲት 66 አብዮት ያነሳውን ሀገራዊ ጥያቄ ለመመለስም ሆነ የኢትዮጵያን ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብት ለማክበር ፍላጎቱም፣ የሞራል ብቃቱም ሆነ የታሪክ ተልዕኮ ሊኖራቸው አይችልም።

ከሠላሳ አራት ዓመታት በኋላ አሁንም የዴሞክራሲ ሥርዓት የውሃ ሽታ ሆኗል። መከራው፣ ድኅነቱ፣ ረሀብ እርዛቱ፣ በሽታው፣ ስደቱ፣ ጦርነት እንግልቱ እንዲሁም እስራቱ፣ በዚያው ልክ እየጨመረና እየባሰ ከመሄድ በስተቅር ሊቀነስ አልቻለም። ከሀገሪቱ ዜጋ መካከል ከመቶ ሰማኒያ አምስቱ፣

በእርሻ የሚተዳደር መሆኑ ቢታወቅም፣ መሬት በአራሹ እጅ በባለቤትነት እስካሁን አልገባም፡፡ ይህ ሁኔታ ለርሀብና ለድኽነቱ ዓይነተኛ ከሆኑት ምክንያቶች የመጀመሪያውን ቦታ ይዟል፡፡ የፖለቲካውን የኢኮኖሚውንና የማኅበረሰባዊውን ሁኔታ ለሚከታተለው አስታዋይ ዜጋ፣ በሁለንተናዊ መልኩ የከፋ የተበላሸ መሆኑ በሚገባ ይረዳዋል፡፡ የዚህ ሁሉ ጦስ የሆነው፣ በብሔረሰብ ልዩነት ላይ የተመሠረተ አስተዳደር በመዘረጋቱ ለመሆኑ፣ የሚያከራክር አይሆንም፡፡ የየካቲት አብዮት ከመፈንዳቱ አስቀድሞ የነበረውና አሁንም ያለው የእኛ ራዕይ የተመሠረተው ፣ በጊዜና በአፍለኛ ፖለቲካ ሊሻር በማይችል፣ በሀገራችንና በሕዝባችን ቋሚና መሠረታዊ ጥቅም ላይ ነው፡፡ ይህ መሠረታዊ አቋማችን ከወያኔ ቡድን ጋር በማይታረቅ ተጻራሪነት እንድንቆም አድርጎናል፡፡ ከወያኔ ጋር ያለን መሠረታዊ ልዩነትም ይኸው ነው፡፡ በአመለካከት ድረጃ ሀገራችን በበርካታ ሺህ ዓመታት ርዝማኔ ባለው የትግል ታሪክ ያረጋገጠችው የራሷ ሰብዕና ፣ የነፃነት ኅልውና ፣ የዜጎቿ አንድነት የግዛት ልዕልና ፣ የነበራት ሀገር ነች ብለን ለዲሞክራሲ ሥርዓትና ለዕድገት ስንታገል፣ ወያኔዎች ግን ፣ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ከአንድ መቶ ዓመት ወዲህ የተፈጠረች የአካባቢ ጎሳዎች ጥርቅም ነች ይሉና ፣ ነዋሪዎቹም፣ በግድ የተገናኙ ስለሆኑ፣ ወደፊት አብረው ለመኖር የሚያስችላቸው ምክንያት የሚያስተሳስራቸው የጋራ ክር የላቸውም ብለው ደምድመዋል፡፡ ቅድሚያ የምንሰጠውም፣ የድርጅታችን የህወሓትን መሠረታዊ ዓላማ በሥራ ለመተርጎም ነው፡፡ በመሆኑም፣ ለእኛ ለወያኔዎች ያልሆነች ኢትዮጵያ ትበጣጠስ ይላሉ፡፡ ዓላማቸውንም በተግባር ለመለወጥ፣ በየክልላቸው ንዑሳን መንግሥታት እየመሠረቱ፣ ተለያይተው መኖር አለባቸው ብለው ተነስተው፣ ሕዝቡን በመርዘኛ ጠባብ ብሔረተኛነት ከፋፍለው ሀገሪቱን እያጠፏት ይገኛሉ፡፡

አንድ ሀገር ሲገነባ በሂደት የተፈፀመን በደል ሆነ ጥፋት፣ ዛሬም እያደሱና ማስለቀሻ እያደረጉ፣ በታሪክ የተገነባውን የሕዝብ አንድነት፣ ታሪክ ያቆየውን የሀገራችን ኅልውና ፣ ውኅደትና ፍቅር፣ትብብር ጥንካሬ ሳይሆን ፣ ቁርሾና ክፍፍልን በማራገብ ትላንት ለተፈፀመው ሁሉ፣ የዛሬው ትውልድ እንዲፋጅ የነገው ተተኪ ትውልድም በደም አለባ ተዘፍቆ እንዲጫረስ ያዘጋጁታል፡፡ ይህ ወያኔ የሚቀብረው፣ ጊዜውን እየጠበቀ የሚፈነዳ የክፍፍል ቦምብ ሁሉ መክሸፍ ይኖርበታል፡፡ ይህንም ለማድርግ ደግሞ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ችሎታውም ኃይሉም እንዳለው ግልፅ ነው፡፡ የሚቀጥለው ተተኪ ትውልድ በወያኔ የብሔረሰብ ክፍፍል አጀንዳ ወጥመድ እንዳይገባ አስፈላጊው የመከላከል ርምጃ መውሰድ ከወቅቱ የትግል አጀንዳዎቻችን ውስጥ አንዱና ዋናው መሆን ይገባዋል፡፡ ይህ ሊሳካ የሚችለው ደግሞ፣ ለነፃነቱና ለአንድነቱ ቀናዒ ከሆነው ከመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ጎን በመቆም ነው ፡፡ የኢሕአፓ መሠረታዊ የታሪክ ግንዛቤ ፣ መነሻው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ክብር፣ የነፃነት፣ የሉዓላዊነት፣ የታሪክና የባህል መግለጫ የሆነው፣ በረዥም ታሪካዊ ሂደት እየተገነባ የተጓዘው የሕዝቧ የጋራ ታሪክ ሲሆን ፣ መድረሻችን ደግሞ፣ በብሔረሰቦች እኩልነትና አንድነት ላይ የተመሠረተው ጠንካራ፣ የበለፀገች፣ፍትኃዊ ሥርዓት የሰፈነባት ኢትዮጵያን መገንባት ይሆናል፡፡ የመልካም ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር መርህ ፣ የሀገራችን መንግሥታዊ ፍልስፍና መሆኑን አምኖ ፓርቲያችን በፅናት ታግሏል፡፡ ይህ የኢሕአፓ መሠረታዊ ዓላማና መተከላዊ አቋም፣ የፀረ አንድነትና የአድህሮት ኃይላት እንደ እግር እሳት ሲያቃጥላቸው ቆይቷል፡፡ በዚህ ምክንያት፣ ፓርቲው፣ ከጠባብ ብሔረተኞችና ከፋሽስታዊው ደርግ ይህ ነው የማይባል ጥቃት ደርሶበታል፡፡ ወደፊትም የኢትዮጵያን መፈራረስ ከሚመኙ ክፍሎች ተመሳሳይ ጥቃት እንደሚሰነዘርበት የሚጠበቅ ቢሆንም፣ ማነኛውንም መሥዋዕት በመክፈል፣ ኢሕአፓ ሕዝባዊ ዓላማውን ከግብ እስኪደርስ ድረስ ለጠላቶቹ ጥቃት ከማይበገረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ተሰልፎ፣ ትግሉን ይቀጥላል፡፡ ይህ ደግሞ ከየካቲት 66ቱ የኢትዮጵያ አብዮት የተረከብነው ብሔራዊ ተልዕኳችን ብቻ ሳይሆን ፣ለተልዕኮው መሳካት ሲታገሉ ከተሰውት ሰማዕታት ጓዶቻችን የተረከብነው የቃል ኪዳን አደራም ጭምር ነው፡፡

ለአለፉት ሠላሳ አራት የትግልና የመሥዋዕት ዓመታት በሀገራችን የፖለቲካ መልከአ-ምድር ሦስት የተለያዩ ሥርዓተ መንግሥታት ተፈራርቀዋል፡፡ የመጀመሪያው ለሥርዓቱ ማጠየቂያ ያደረገው ከዕሥራኤላዊው የሰሎሞን ስርወ መንግሥት በዘር ሀረግ የወረስኩት ሥልጣን አለኝ የሚል ነበር፡፡ ከዚህም በመነሳት፣ ሰብዕናው የማይደፈር፣ ሥልጣኑ የማይገሰስ አድርጎ በመቁጠር የፈላጭ ቆራጭ አምባገነን አገዛዝ አዋቅሮ ለግማሽ ምዕተ ዓመት ያህል የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደ

ገል ቀጥቅጦ፣ እንደ ሰም አቅልጦ በድኅነትና በርሀብ ሲገዛ ቆየ፡፡ ተበዝባዥ ዜጎች፣ ተጨቋኝ ሕዝቦች ሁሉ፣ የመከራቸው የግፍ ጽዋ ሞልቶ ሲገነፍል፣ በጨቋኞቻቸው ላይ ተባብረው ላፈጠጠው ፍልሚያና ለማይቀረው ሕዝባዊ ድል በመነሳት በወርኃ የካቲት የጉልታዊ ሥርዓቱን ገርስሰው ጣሉት፡፡

" በአንድ እንደሚነሳ ተበዝባዡ ሁሉ፣
ለማይቀረው፣ ለማያጠራጥር ድሉ"

የተባለውን ሐቅ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሞላ በተጨባጭ አስመስክሮ የየካቲትን አብዮት በፋና ወጊነት አረጋገጠ፡፡ ያ ፈላጭ ቆራጭ ያረጀ-ያፈጀ አድኃሪ ሥርዓትም ወደማይቀርለት ግብዓተ መሬት ወረደ፡፡ ይህ አፈጻጸም፣ አብዮት በተካሄደባቸው ሀገሮች ሁሉ በዋና መልኩ የተከናወነ ነው፡፡ ይህ ሕዝባዊ አመፅ ያስከተለውን አብዮታዊ ሁኔታ በሚገባ እያስተናገደ የሚመራው ጠንካራ የተደረጀ ሕዝባዊ ኃይል ባለመገኘቱ፣ የአምባገነኑ ሥርዓት አስጠባቂ የነበሩና እስከ መጨረሻው ደቂቃ ድረስ ለሥርዓቱ ታማኝነት ሲምሉ-ሲገዘቱ የቆዩ ጥቂት መኮንኖች፣ የሕዝቡን ድል በመንጠቅ ወታደራዊ አምባገነ አገዛዝ አቋቁመው ያን መከረኛ ሕዝብ ለአስራ ሰባት ዓመታት ለመከራና ለግፍ የጨለማ ዘመን ዳረጉት፡፡ ሕዝቡን ከድተው፣ ጨኸቱን ነጠቁት፡፡ አሮጌው አምባገነንም፣ በአዲስ የወታደር ጨፍጫፊ ሥርዓት ተተካ፡፡ እነኝህ የፊውዳሉ የጦር መኮንኖችም በበኩላቸው፣ ለአመጣጣቸው ማጠየቂያ ለሥልጣናቸው መቆናጠጫ እንዲሆናቸው መነሻ አድርገው የተጠቀሙበት ከሕዝብ የነጠቁትን መፈክርና ጥያቄ ነበር፡፡ ሕዝቡ ለዴሞክራሲ ሲታገል፣ መኮንኖቹ ደግሞ የዴሞክራሲን ጭላንጭል ሁሉ ደብዛውን አጠፉት፡፡ ለአስራ ሰባት ዓመታት የኢትዮጵያን ሕዝብ፣ ወንድ ሴት ህፃን ፣ ሽማግሌ፣ ነጋዴ ገበሬ፣ ወታደር ባላገር፣ ምሁራን መምህራን ፣ ተማሪ አስተማሪ፣ እስላም ክርስቲያ ፣ ሌላውንም የኅብረተሰብ ክፍል ሳይለዩ በጅምላ ጨፈጨፉት፣ በሽብር መተሩት፤ አሰሩት፣ አሰደዱት፣ አስራቡት፣ አሳዘኑት፣ የድኻም ድኻም አደረጉት፡፡ በመጨረሻም ሀገሪቱን አጥፍተው ለበላዒ ሰብና ሀገር አጥፊ ጎሰኛ ቡድን አስረክበው፣ እነርሱም ልክ ከእነርሱ በፊት እንደነበረው ፊውዳል ሥርዓት ከስመው ቀሩ፡፡ አሁን ላለው የሀገሪቱ አስከፊ ሁኔታም ሁሉን ነገር አመቻችተው እንደ ጉም በነኑ፡፡ አጥፍተው ጠፉ፡፡

ወታደራዊ አምባገኑን ሥርዓት የተካውም፣ ወያኔ፣ ከላይ ከተጠቀሱት ሁለት የአምባገነ ሥርዓት አራማጆች በመነሻም ሆነ በመጨረሻ ዓላማና ግቡ ፈፅሞ የተለየ ነው ፡፡ መነሻ አድርጎ የጀመረው፣ የሀገሪቱን ነባር አካል የሆነውን አንድ ክፍለ ሀገር፣ ለብቻው ከልሎ በመገንጠል ነፃ ለማውጣትና የተለየ ሪፑብሊክ ለመመሥረት ነበር፡፡ የወያኔ አመራሮች ፣ ከሁሉ አስቀድሞ ፀረ ኢትዮጵያ መሆናቸውን በተግባር ያስመሰከሩት፣ ደርግ ጥሎላቸው የሸሸው የሀገሪቱ ብሔራዊ የመከላካያ ሠራዊትና ሌሎች ብሔራዊ ተቋማትን በማፈራረሳቸው ነበር፡፡ የወያኔዎቹ ወደ ሥልጣን የመቆናጠጫ ማጠየቂያቸው፣ የብሔር ነፃ አውጭዎች ነን የሚል ሲሆን ፣ በምንም መመዘኛ ቢመዘኑ የኢትዮጵያ ብሔራዊ አጀንዳ ያልነበራቸው፣ አሁንም የሌላቸው ወደፊትም ሊኖራቸው ይችል ይሆናል ተብለው የማይጠረጠሩ መሆናቸው ነው፡፡ ይህ ማንነታቸው ደግሞ በመሠረታዊ መልኩ ከእነርሱ በፊት ከነበሩት ሁለት አምባገነን ሥርዓቶች በዓይነትም ሆነ በባኅርይ በእጅጉ ይለያቸዋል፡፡ ወያኔዎቹ፣ በትውልድና በዜግነት ኢትዮጵያውያን መሆናቸው ባይካድም፣ ፀረ ኢትዮጵያ በመሆን የሚሠሩትን እኩይ ተግባር የተገነዘበ ዜጋ ማንነታቸውንና ለምንስ እንደመጡ በትክክል ይረዳቸዋል፡፡ ለምን ቢባል፣ ከምኒልክ ግቢ ከገቡ በኋላ እንኳን የፈፀሙትን ብሔራዊ ወንጀል በሙሉ ስንታዘብ፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ቀርቶ፣ በዓለም ደረጃም የታወቀና የተመዘገበ በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ ወያኔ ምንነትና ማንነት በሚገባ የሚያወቀውን በተጨማሪ ለማወቅና ለመገምገም ጊዜውን የሚያጠፋ ሳይሆን ፣ የመጀመሪያ አጀንዳ ወይም ግቤ ብሎ ትኩረት ሰጥቶ የሚታገለው፣ ልክ የዛሬ ሠላሳ አራት ዓመት የካቲት 66 የነበረውን ጨቋኝ አገዛዝ እንደ አስወገደ ሁሉ፣ ዛሬም ተባብሮ ወያኔን በማስወገድ፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መመሥረት ነው፡፡ የኢሕአፓም ዓይነተኛ ዓላማና ግብ ይኸው ነው፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ የወያኔን የሀገር ማጥፋት ርምጃ መግታትና ኢትዮጵያን ማዳን ተልዕኳችን ይሆናል፡፡ አትዮጵያ እንደ ሀገር ዜጎቿም እንደ ሕዝብ መኖር አለባቸው፡፡ ይህ ግብ ደግሞ የኢሕአፓ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ኢትዮጵያዊ አልፋ - ኦሜጋ፣ ባሕረ -ኃሳብ ዓላማ ነው፡፡

ይህን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ኢሕአፓ የኢትዮጵያ ሕዝብ የስድሳ ስድስቱ የካቲት ዓብዮት መንፈስ ዓላማ አንግቦ በፅናት ለመታገል የቻለው ዋናው ምክንያት፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ የማይበገር የነፃነት ዓላማና ግብ በማመኑ ነው:: ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ያለው ጠንካራ ትስስር የተመሠረተውም፣ በዜግነታችን ብቻ ሳይሆን፥ በባኅርይ በተግባር፣ በዓላማና ግብ፣ በባህል በዕምነት፣ በታሪክና መስተጋብር፣ በወደፊቱ ተስፋና ራዕይም ጭምር ነው:: ይህ መሠረታዊ ሐቅ ኢሕአፓን ከወያኔዎች ይለየዋል::

የየካቲትን ስድሳ ስድስት አብዮት ሠላሳ አራተኛው ዓመት በምንዘክርበት በአሁኑ ወቅት መሠረታዊ የሆኑ ጉዳዮችን ማንሳት እንገደዳለ :: ከሠላሳ አራት ዓመታት በኋላ፣ አሁንም የኢትዮጵያ ሕዝብ አምባገነኖች በመፈራረቅ ከጣሉበት የጭቆና አገዛዝ አልተላቀቀም:: የኢትዮጵያ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ የማኅበራዊ ሁኔታዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሱ፣ ወደ አዘቅት እየወረዱ ሄዱ እንጂ የተሻሻሉበት ሁኔታ አልታየም:: ሀገራችን ከ34 ዓመት በፊት እንደ ነበረችው አሁንም ከዓለም የመጨረሻ ደኻ አገሮች መካከል አንዷ ሆና ተፈርጃለች:: የሕዝቡ የኑሮ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ አስከፊነቱ ፣ አሰቃቂነቱ እየጨመረ መጣ እንጂ የቀነሰበት ሁኔታ አይታይም:: የሀገራችንና የሕዝባችን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ይበልጥ እየተወሳሰቡ ከመሄዳቸውም ሌላ ራሱ የኢትዮጵያ ህልውና አስጊ ደረጃ ላይ የደረሰበት ሁኔታ ነው የሚታየው:: ባጭሩ የካቲት 66 አብዮት ያነሳቸው ጥያቄዎች አሁንም በአግባቡ ምላሽ ያገኙበት ሁኔታ አይታይም:: ኸረ ለመሆኑ እነኝህ ሶስት ተፈራራቂ አምባገነን ሥርዓቶች ለምን በሕዝቡ ላይ በየተራ ጭቆና ሊያካሂዱበት ቻሉ? የኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃስ እስከመቸ ድረስ ነው የተፈራራቂ አምባገነኖችን ጭቆና እንዲሸከም የሚፈረድበት? ሌላ አራተኛ አምባገነን ደግሞ እንዳይመጣስ ምን መደረግ አለበት? የሀገራችንስ የወደፊት ዕጣ ምን መልክ መያዝ አለበት? እነዚህ መሠረታዊ ጥያቄዎች ተገቢ መልስ ያስፈልጋቸዋል:: ጥያቄዎቹን በማያሻማ መልኩ ለመመለስ ደግሞ በግድ አንድ ሌላ ቁልፍ ጥያቄ መልስ ማግኘት እንዳለበት ምንም ብዥታ ሊኖር አይችልም:: ይኸውም፣ የወያኔ ከሥልጣ መወገድ ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ አንገብጋቢና ወሳኝ መሆኑ ነው::

ከዚህ ቀደም የካቲት 66ን በመዘከር በወጣው ዴሞክራሲያ (መጋቢት 1998) ያሰፈርነው ሐቅ ዛሬም ቢጠቀስ ወቅታዊነቱን አላጣም::

" ከየካቲት 66 እስካሁን ፣ ከሚያዝያ 64 እስካሁ ኢሕአፓ ያለፈው የሕዝብ የትግል ተመክሮ ሲገመግም የአገዛዙን ይዘት ሲያጤን ፣ እንደ አሁኑም አገዛዝ ከሕዝብ የተጣላና የተነጠለ አለመኖሩን ሲያይ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የተረጨው የክፍፍል መርዝ ጉዳቱ እንዳለ ሆኖ፥ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ነቅቶ ለመብቱ ለመታገል ቆርጦ መነሳቱን ይገነዘባል:: አገዛዙ እንዳለፈው ተንሰራፍቶና ተደላድሎ ሊገዛ ሳይችል ሲቀር፤ ሕዝብ በቃኝ ብሎ ለለውጥ ሊያምፅ ሲነሳ ሀገሪቷ ያረገዘችውን ለውጥ ለመገላገል መቃረቧ እሙን ነው:: በአዋላጅነት የሚያገለግሉ ድርጅቶች መኖራቸው አስፈላጊና ጤናማ መሆኑም የሚካድ አይደለም:: የአስተባባሪ ድርጅት ያለህ የሚለውን ሕዝባዊ ጩኸት አዳምጠው በተግባር በተጨባጭ ትግል ግንባር ቀደም ሚና ሊጫወቱ ዝግጁ ከሆኑት ጋር ኢሕአፓ በማበር የሕዝብ ትግል ድል ለማረጋገጥ ዛሬም ቃል ኪዳኑን አድሶ ተሰልፏል:: ትግላችን የጋራ፤ ግባችን አገዛዙን ማስወገድ፤ ተልዕኮው የጋራ፣ ትግላችን መልከ ብዙ፣ ዓላማው ግቡን ሳይመታ የማይቆም በአዲስ ዴሞክራሲያዊ መሠረት ላይ ኢትዮጵያን በጋራ ለመገንባት:: ከሁሉ በፊት ግን ከአገዛዙ መላቀቅ::"

የዳግማዊ የካቲት የድል ታሪክ ይፃፍ!
እናቸንፋለን !!